# ሙሽሪት ሙሽራው







ምንኛ ተካሰች፥ ውቢቱ ፋሲካ
ድርሻዋን አገኘች፥ ታንድዬ ተሻርካ፤

ከበዓልም በዓል፥ ግጥሙ ተፋሲካ
እልቡ ተገኘች፥ ተገነት ተልካ፤

ካስዬ ትጉሁ፥ የግዜር አገልጋይ
ምንዳውን አገኘ፥ ተላይ ተሰማይ፤

ሙሽሪት ሙሽራው፥ ያጥቢያ ኮከባችን
በተክሊል ከበሩ፥ ደስ አለው ልባችን፤

አባ አብርሃም ደጉ፥ አበ ነፍሳችን
እንኳን ደስ አለዎት፥ ጸናች ቤታችን፤
ኮትኩተው አርመው፥ ፍሬ ሁን ያሉት
የተስፋን ፋሲካ፥ ያንተነህን ካሣ
ኦስሎ እምብርቱ ላይ፥ በስሎ አገኙት፤

ብረሪ አንቺ እርግብ፥ ተበተስኪያን ጓሮ
ይሽብሽብ፥ ይወረብ፥ ይመታ ከበሮ
ብረሪ አንቺ እርግብ፥ ጸናጽል ይዘሽ
ኦስሎ፥ እስታቫንገር፥ ወይ በርገን እያልሽ
የስትኮልሙን አባት፥ ቄስ ጌጡን ይዘሽ
ጥኡመ ልሳኑን፥ መጋቤ ምስጢሩን አባ ቴድሮስን
እጅዎ ተምን  ብለሽ፥ ቅኔ አስገብሪልን
እንኳን ደህና መጡ፥ እያልሽ ተቀኚልን፤

ብረሪ አንቺ እርግብ፥ ገበታ ስሪልን
ሙሽራው ሙሽሪት፥ እያልሽ ዘምሪልን፤
ዲያቆን አንዳርጌና ዲያቆን አብርሃምን
ባለሳምንት አርገሽ፥ ቃል አስገቢልን፤
ለኒህ ለሚዜዎች፥ ልብ ስጪልን...

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ለመጋቤ ሙሴ፥ ጽዋ አድርሺልን
ለሁሉም መያዣ፣
ዲያቆን ዘላለምን ዋስ አስጠሪልን፤

ብረሪ አንቺ እርግብ፥ ባዳራሽ በልፍኙ
ፋሲካን ካሰዬን ብለው የታደሙ፥
ብለው የተገኙ፤
ይህን ሠርግ ሠርገው፥ ደግሰው የዳሩ
የግዜር ቤተሰቦች፥ ምርቃት ይቸሩ፤

ጎጇቸው ጎጆ ይሁን፥ ያብርሃም የሣራ
ይዘመር ይወረብ፥ ይሽብሽብ በተራ፤
*“የኛ ሙሽራ ቤላ ቤላ፥ አንቺ ልጅ ማር ወለላ*
*የኛ ሙሽራ ቤላ ቤላ፥ አንተ ልጅ ከረሜላ”*
ከዚህ የበለጠ ምናለ ረድዔት፥ ምን አለ አዝመራ
ባንድዬ ቸርነት፥ ሠርግ እንዲህ ተሠራ!

በአበራ ለማ
ለወ/ት ፋሲካና ለዲያቆን ካሣዬ ሙሽርና ሚያዝያ 18
ቀን 2001 ዓ.ም. ተቋጨ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com